
Confidential Student Performance Report
Colorado Measures of Academic Success
Spring 2019
Grade 4
English Language Arts/Literacy
Performance Level Descriptor - Met Expectations

# የኮሎራዶ የትምህርታዊ ስኬት መለኪያዎች

## የተማሪን የትምህርት ስኬት ለመደገፍ የCMAS ውጤት ሪፖርትን መጠቀም

COLORADO Department of Education

www.cde.state.co.us

የኮሎራዶ የትምህርት ስኬት መለኪያዎች (CMAS) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ እና ሶሻል ስተዲስ ምዘናዎች ከኮሎራዶ የትምህርት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) ጋር የሚተካከሉ ሲሆኑ እንደ ጥልቅ አስተሳሰብ እና ችግር-ፈችነት ያሉ ውስብስብ ክህሎቶችን ይለካሉ። የውጤት ሪፖርት የCMAS ፈተናን ለወሰደ ለእያንዳንዱ ተማሪ ይዘጋጃል። ሪፖርቶቹ ወላጆች ልጆቻቸው የኮሎራዶ ትምህርት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) የሚጠይቋቸውን መስፈርቶች እያሟላ እና ለኮሌጅና ከምረቃ በኋላ ለሥራ ትክክለኛ መስመር ላይ መሆኑን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ የሚያደርጉ መረጃዎችን ይይዛሉ።

## ማስታወስ የሚገቡዎ ነገሮች

- የCMAS ፈተናዎች ተማሪዎች ከምረቃ በኋላ ለሥራ ትክክለኛ መስመር ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ልክ እንደ ፍኖተ-ካርታ ከሆነው ከ ኮሎራዶ ትምህርት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) ጋር የሚተካከሉ ናቸው። በስፕሪንግ 2018 ውስጥ የስቴቱ የትምህርት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) የስቴቱ ሕግ በሚጠይቀው መልኩ ተሻሽለዋል። የተከለሱት የኮሎራዶ የትምህርት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) እከ 2020-21 የትምህርት ዘመን ድረስ ሥራ ላይ የማይውሉ ሲሆን የስቴት ፈተናዎች እንዲተካከሉ ወይም እንዲጣጣሙ የሚደረገው በዚያ ጊዜ ይሆናል። የት/ቤት ዲስትሪክቶች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ወደ አዲሶቹ ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) እና የስቴት ፈተናዎች ለመሸጋገር ሌላ አንድ ዓመት አላቸው።
- የCMAS ፈተናዎች በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚሰጡ ሲሆኑ የልጅዎን እድገት/ለውጥ ሙሉ ምስል ለመስጠት ከሪፖርት ካርዶች፣ ከክፍል ውስጥ አፈጻጸም እና የመምህራን ግብረ-መልስ ጋር ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አንድ አመላካች ብቻ ናቸው።
- ፈተናዎቹ ተማሪዎቹ ዛሬ የሚፈልጓቸውን - እንደ በጥልቀት ለማሰብ መቻል እና ውስብስብ ችግሮችን ማቃለል ያሉ ክህሎቶችን ይለካሉ።
- ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ተማሪዎች የክፍል-ደረጃ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ማወቅ ወላጆች እና መምህራ ተማሪዎቹን ለኮሌጅ እና ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ለሥራ የተሻለ እንዲያዘጋጁቸው ጊዜ እንዲያገኙ ያደርጋል።

## ልጄን እንዴት መደገፍ እችላለሁ?

- ልጅዎ የክፍል-ደረጃ ግቦችን እያሟላበት/እያሟላችበት ወይም እየላቀበት/እየላቀችበት ያለን ትምህርት ለማዳበር ስልቶችን (ስትራቴጂዎችን) ለመለየት ከልጅዎ መምህር ጋር በጋራ ይሥሩ። እንደዚሁም የልጅዎ መምህር የልጅዎን አፈጻጸም በሚያስፈልግበት ሁኔታ ለማሻሻል ግብዓቶችን/አቅርቦቶችን ለመለየት ሊረዳዎት/ልትረዳዎት ይችላል/ትችላለች። ተማሪዎች ክህሎቶቻቸውን ለመለማመድ ሊያግዙ ከሚችሉ ውስጥ የማጠናከሪያ ትምህርት፣ የድህረ-መደበኛ ትምህርት ሰዓት ፕሮግራሞች ወይም የቤት ውስጥ ተግባሮች ይገኙባቸዋል።
- <u>የፈተና ውጤቶች የእድገት አንድ አመላካች ብቻ እንደሆኑ</u> ለልጅዎ ያረጋግጡለት/ላት።
- በቤት ውስጥ የትኞቹን ክህሎቶች ማጠናከር እንዳለብዎ ይወስኑ። የልጅዎ ውጤት ሪፖርት ላይ ዝርዝር የክህሎቶች መግለጫ መሻሻል የሚፈልጉ መስኮችን ለመለየት ከፍተኛ መነሻ ነጥብ በመሆን ያገለግላል።
- ስለኮሎራዶ የትምህርት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) እና የውጤት ሪፖርቶችን ለመረዳት መመሪያን ጨምሮ ከእነሱ ጋራ ስለተካከሉ ምዘናዎች እና በተደጋጋሚ ስለሚነሱ ጥያቄዎች ተጨማሪ መረጃዎችን በዚህ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ፦
www.cde.state.co.us/communications/resourcesforparents

## የበለጠ የት መረዳት እችላለሁ?

የኮሎራዶ ጠንካራና የትምህርት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) የተዘጋጁት ሁሉም የኮሎራዶ ተማሪዎች ለኮሌጅ እና ለሥራ ላይ ስኬታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነበር። የኮሎራዶ ምዘናዎች ከእስቴት ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) ጋር የተካከሉ/የተጣጣሙ ሲሆኑ ተማሪዎች በረጅም ጊዜ ውስጥ ምን ዓይነት አፈጻጸም እና እድገት እንዳላቸው እና በዲስትሪክቱና በስቴቱ በሞላ ካሉ እኩዮቻቸው ጋር እንዴት እንደሚወዳደሩ ወይም ምን ላይ እንደሚገኙ አስተማሪዎች እና ወላጆች እንዲያውቁት ይረዳሉ።

የበለጠ ለመረዳት፦ Www.cde.state.co.us/communications/resourcesforparents ን ይጎብኙ